# ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት?

ርእዮት በተባለው ፕሮግራም በኣቅራቢው፣
በኣቶ ቴዎድሮስና፣
በፕሮፌሰር በረከት ሃብተስላሴ በተካሄደውን ቃለመጠይቅ፤

"ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች ወይ?"

ለሚለው ጥያቄ ፕሮፌሰሩ ሲመልሱ፤ ለኤርትራ ነፃነት ትግል መሣሪያ ሆኖ ማገልገሉን ኣምነው፣ "ኣከራካሪ ጉዳይ ነው።" ሲሉ ፕሮፈሰሩ ጉዳዩን ኣድበስብሰው ኣልፈውታል።
ፕሮፌሰር በረከት ሃብተስላሴ ቃለመጠይቁን ሲደመድሙ ለዛሬው ትውልድ የማስተላልፈው ምክር ከምንለያይበት ነገር ይልቅ በሚያስተባብረን ብናተኩር፣ ከሚያጣላን ጉዳይ ይልቅ በሚያፋቅረንና በሚያቀራርበን ላይ ብንነጋገር ይሻላል፣ ኣንድ ሕዝብ ነን፣ ብዙ የሚያኮራ ባህልና ታሪክ ኣለን፣ ለወደፊትም ኣንድ እንደምንሆን ተስፋ ኣለኝ ይላሉ።
ይህ ሁሉ መልካም ሆኖ እያለ፣ ከዚህ በማስከተል የማቀርበው ጽሑፍ 'ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች' ለሚባለው ሓሰት መልስ ነው። ይህንን ያነበበ ሰው ዳግመኛ ይህንን ሓሰት ሲሰማ ዝም ብሎ እንዳይቀበለው ይረዳሉ የምላቸው ዋና-ዋና ነጥቦችን ከዚህ ቀጥሎ ኣቀርባለሁ። ይህንን ከማቅረብየ በፊት ግን ኣቶ ቴዎድሮስ በቃለ መጠይቁ ጊዜ ኤርትራ ቅኝ ግዛት እንዳልነበረች ለማስረዳት ያቀረባቸው ጥሩ ነጥቦችን ማንሳት ደግ ነው።
ነጥቦቹ፡- በኤርትራ ከሌሎች የኢትዮጵያ ክፍለሃገሮች የበለጠ እንጂ ያላነሰ የተቋማት ቁጥር ተተክለው እንደነበር፣ ከዚህም ሌላ ኣንድ ሃገር የገዛ ኣካሉ የነበረውን መሬት ከቅኝ ገዢው መልሶ ሲወስድ ወደ ጥንት ቦታው ተመለሰ ይባላል እንጂ እንዴት ቅኝ ሆነ ሊባል ይቻላል? ለምሳሌ ሆንግ-ኮንግ ከረዥም የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ዘመን ወደ እናት ሃገሯ ወደ ቻይና መቀላቀዋ፣ የቻይና ቅኝ ግዛት እንዳልሆነች በማለት ሊያስረዳ ደህና ኣድርጎ ተከራክሯል።
እነዚህ እንዳሉ ሆነው፣ ከዚህም ሌላ ሊነሱ የሚገባቸው ዓበይት ነጥቦች ኣሉ።
1) በሃይለሥላሴ ዘመን በነበረው ፓርላማና በደርግ ዘመን በነበርው ኢሰፓ የኤርትራ የሕዝብ ተወካዮች ከየወረዳውና ከየኣውራጃው እየተመረጡ ኣባል ሆነው ያገለግሉ እንደነበር፣ ይህም እንደ ሁሉም የኢትዮጵያ ክፍለሃገሮች እኩል እንጂ ምንም ቅኝ ግዛት የሚያሰኝ ልዩነት እንዳልነበር ያሳያል። 2) በሃይለሥላሴ ዘመንና በደርግ ዘመን ኤርትራውያን በተለያዩ የመንግሥት መዋቅር እየተንቀሳቀሱ በመሥራት ከማንም ኢትዮጵያዊ የበለጠ እንጂ ያላነሰ ሚና የያዙ እንደነበሩ የማይካድ ሓቅ ነው።
ለዚህም ዋና ማስረጃ ፕሮፌሰሩ ራሳቸው በሃይለሥላሴ ዘመንና በደርግ ዘመን ከፍተኛ ባለ ስልጣን እንደነበሩ የማይክዱት ሓቅ ነው። በተጨማሪም መጥቀስ ካስፈለገ፣ እኔ ልጅ ሆኘ የዓድዋ ኣገረ-ገዥ ኮሎኔል (ኋላ ጀነራል) ኢሳያስ ገ/ሥላሴ የተባሉ ኤርትራዊ ሰው ነበሩ። ከሳቸውም ሌላ ብዙዎች ኤርትራውያን በመላው የሃገር ኣገዛዝ፣ እስከ ምኒስተር ደረጃ፣ በጦር ሃይሎችም ከጀነራል ኣንስቶ እስከ ተራ ወታደር፣ እስከ መጨረሻውም የርእሰ-ብሔር ቁንጮ የወጡት ጀነራል ዓምዶምን ብንወስድ፣ በፍጹም ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች የሚባለው ነገር ምንም የማያከራክር ውሸት መሆኑን ለማየት ይቻላል።
ይህንን የማይቀበል ሰው ካለ፣ ኣንዲት ኣፍራሽ የምትሆን ማስረጃ ሊያርብልኝ ይችላል። ይኸውም፤ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይ፣ የስፓኛ፣ የፖርቱጋል... ወዘተ፣ ቅኝ ግዛት ከነበሩት ሃገሮች ከኣንዳቸውም ቢሆን፤ ከህንድ፣ ከናይጀርያ፣ ከኣልጀርያ... ወዘተ፣ ከቅኝ ግዛቶች ወደ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ወይ ስፓኛ ወስዶ ኣገረ-ገዢ ያደረገ ካለ፣ ለማስረጃ ቢቀርብልኝ፣ እኔ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች ብየ መቶ-በመቶ እቀበለዋለሁ። እስከዚያ ድረስ ግን ይህ ጉዳይ ምንም ኣከራካሪ እንዳልሆነ ለፕሮፌሰር በረከትና ሌሎችም የተሳሳተ ኣስተሳሰብ ለያዙ ሰዎች ሀሉ መግለጽ እፈልጋለሁ። ይህ ውሸት ከእንግዲህ ወድያ ቢያበቃ ደግ ነው።
ይህ ለኤርትራ ነፃነት ትግል ሲባል የተጠነሰሰ ሓሰት ነው ተብሎ ከታመነበት ወደፊት ለመራመድ የሚቻለው ውሸቱን ኣጋልጦ፣ በሓቅ መሰረት ተረግጦ ነው እንጂ ይህን ሓሰት ተመርኩዞ ወደፊት ለመሄድ ኣይቻልም። ስለዚህም ነው በዚህ ለማትኮር የፈለግሁት።

ፕሮፌሰር በረከት ሃብተሥላሴ በመቀጠል፤ የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ በኮንፌድሬሽን ኣብሮ ሊኖር ምኞትና ተስፋ ያላቸው መሆኑን በተደጋጋሚ ገልጸዋል። ይህም በጣም ደስ የሚል ሓሳብ ቢሆንም እንኳን፣ ይህንን የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበርን የሚባለውን ሓሰት እያድበሰበሱና፣ 'ኣከራካሪ ጉዳይ ነው' እያሉ በማንሸራሸር ኣንድነት ሊገኝ ፈጽሞ ኣይቻልም። ዘላቂ ኣንድነት ሊገኝ ከሆነ በሓቅ የተመሰረተ ኣንድነት መሆን ኣለበት። ፕሮፌሰሩ የሕግ ምሁርና ሊቅ ናቸው፣ እሳቸው ይህንን ነገር ሓሰት ነው ብለው ካላወገዙት፣ ያልተማረው ምሃይም ሰውማ ሓቅ ነው ብሎ ነው የሚቀበለው።

ኤርትራ ኣሁን ለገባችበት ዓዘቅት ምክንያቱ ይህንን እና ሌሎችም ብዙ መሰረት የሌላቸው ሓሰቶች ይዛ በመነሰቷ ነው። ቅኝ ግዛት የሚባለው ሓሰት የተጀመረው ቀንድ ያበቅልና፣ ቅኝ ግዛት ብቻ ሳይሆን ለነፃነት መውጣት በተካሄደው ምርጫ ላይ ደግሞ፣ ኣማራጮቹ፤ "ነፃነት ወይም ባርነት" የሚሉ ነበሩ። ይህም ማለት ኤርትራ በኢትዮጵያ ቅኝ ከመግዛቷዋም ታልፎ፣ ኤርትራውያን ምንም መብት እንደሌለው ሰው፣ "ባርያ" ነበሩ የሚል ዓይን ያወጣ ውሸት ለምርጫ እንዳቀረቡት መታወቅና ሓሰትነቱን ኣምኖ መቀበል ያስፈልጋል።

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ሓሰቶች እንደፕሮፌሰሩ ለመሰሉት ሰዎች ኣከራካሪ መሆን ኣይገባቸውም። ፕሮፌሰር በረከት በነበራቸው ልዩ ሚና፣ ማለትም እስከ ኣገረ ገዢነትና እስከ ምክትል እንደራሴነት መዓረግ ተሾመው በኢትዮጵያ ያገለገሉ በመሆናቸው፣ የእነዚህ ነገሮች ሓሰትነት በግልጽ ለማስረዳ የሚችሉ እና፣ የኢትዮጵያ ሕዝብና የኤርትራ ሕዝብ ከነበረው ስርዓት ስር እኩል ይገዙ እንደነበሩ፣ የኤርትራ ሕዝብም ከሌላው ብሔር የቀለለ እንጂ ምንም የከበደ ጫና እንዳልደረሰበት፣ ይልቅም ሌሎች ብዙ ብሔሮች የባሰ ቀምበር የተጣለባቸው እንደነበሩ ሓቁን መግለጽ የሚገባቸው ሰው ናቸው። ይህንን ግን ኣላደረጉም። ይባስ ብሎ፣ ከፕሮፌሰሩ ተደጋግሞ የተሰማው፣ "ንጉሡ ፌዴረሽኑ ቢፈርስ ምን ይመስልሃል ብለው ጠይቀውኝ፣ 'ጃንሆይ፣ ይህ የተኛውን ኣንበሳ መቀስቀስ ነው' ኣልኳቸው..." እያሉ ስለ ኤርትራ ሕዝብ ኣንበሳነት ለመናገር የተነሱ ነው የሚመስሉ። ይህም ኣዲስ ነገር ሳይሆን፣ ዘወትር ኤርትራውያን ራሳቸውን ለማታለል የሚሉት ሓሰት ነው። ሓቁ ግን ኣንበሳ በራሱ ሓሳብ የሚመራ እንጂ በሌላ እንሰሶች የማይመራ ፍጡር ሲሆን፣ ኤርትራውያን ግን መላው የነፃነት ትግላቸው እንደሚመሰክረው የግብፅ፣ የሊብያ፣ የሶርያ፣ የዒራቅ፣ የሌሎችም የዓረብ መንግሥታት ኢትዮጵያን ለማዳከም መሣርያ ኣድርገው እንደተጠቀሙባቸው ሓቅ እንጂ ምንም የሚያጠያይቅ ጉዳይ ኣይደለም። ኢትዮጵያም እጆችዋን ወደ እግዚኣብሔር ኣንስታ በእነዚህ የዓረብ መንግሥታት መሪዎችና ሕዝቦች የደረሰና የሚደርስም ያለው ፍርድና ቅጣት ዓይን ላለው ሁሉ ግልጽ ነው። ይህ ለኤርትራም ሕዝብ የሚተርፍ ያለ ይመስላልኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት?

ርእዮት በተባለው ፕሮግራም በኣቅራቢው፣ በኣቶ ቴዎድሮስና፣ በፕሮፌሰር በረከት ሃብተስላሴ በተካሄደውን ቃለመጠይቅ፤ "ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች ወይ?" ለሚለው ጥያቄ ፕሮፌሰሩ ሲመልሱ፤ ለኤርትራ ነፃነት ትግል መሣሪያ ሆኖ ማገልገሉን ኣምነው፣ "ኣከራካሪ ጉዳይ ነው።" ሲሉ ፕሮፈሰሩ ጉዳዩን ኣድበስብሰው ኣልፈውታል።

ፕሮፌሰር በረከት ሃብተስላሴ ቃለመጠይቁን ሲደመድሙ ለዛሬው ትውልድ የማስተላልፈው ምክር ከምንለያይበት ነገር ይልቅ በሚያስተባብረን ብናተኩር፣ ከሚያጣላን ጉዳይ ይልቅ በሚያፋቅረንና በሚያቀራርበን ላይ ብንነጋገር ይሻላል፣ ኣንድ ሕዝብ ነን፣ ብዙ የሚያኮራ ባህልና ታሪክ ኣለን፣ ለወደፊትም ኣንድ እንደምንሆን ተስፋ ኣለኝ ይላሉ።

ይህ ሁሉ መልካም ሆኖ እያለ፣ ከዚህ በማስከተል የማቀርበው ጽሑፍ 'ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች' ለሚባለው ሓሰት መልስ ነው። ይህንን ያነበበ ሰው ዳግመኛ ይህንን ሓሰት ሲሰማ ዝም ብሎ እንዳይቀበለው ይረዳሉ የምላቸው ዋና-ዋና ነጥቦችን ከዚህ ቀጥሎ ኣቀርባለሁ። ይህንን ከማቅረብየ በፊት ግን ኣቶ ቴዎድሮስ በቃለ መጠይቁ ጊዜ ኤርትራ ቅኝ ግዛት እንዳልነበረች ለማስረዳት ያቀረባቸው ጥሩ ነጥቦችን ማንሳት ደግ ነው።

ነጥቦቹ፡- በኤርትራ ከሌሎች የኢትዮጵያ ክፍለሃገሮች የበለጠ እንጂ ያላነሰ የተቋማት ቁጥር ተተክለው እንደነበር፣ ከዚህም ሌላ ኣንድ ሃገር የገዛ ኣካሉ የነበረውን መሬት ከቅኝ ገዢው መልሶ ሲወስድ ወደ ጥንት ቦታው ተመለሰ ይባላል እንጂ እንዴት ቅኝ ሆነ ሊባል ይቻላል? ለምሳሌ ሆንግ-ኮንግ ከረዥም የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ዘመን ወደ እናት ሃገሯ ወደ ቻይና መቀላቀዋ፣ የቻይና ቅኝ ግዛት እንዳልሆነች በማለት ሊያስረዳ ደህና ኣድርጎ ተከራክሯል።

እነዚህ እንዳሉ ሆነው፣ ከዚህም ሌላ ሊነሱ የሚገባቸው ዓበይት ነጥቦች ኣሉ።

1) በሃይለሥላሴ ዘመን በነበረው ፓርላማና በደርግ ዘመን በነበርው ኢሰፓ የኤርትራ የሕዝብ ተወካዮች ከየወረዳውና ከየኣውራጃው እየተመረጡ ኣባል ሆነው ያገለግሉ እንደነበር፣ ይህም እንደ ሁሉም የኢትዮጵያ ክፍለሃገሮች እኩል እንጂ ምንም ቅኝ ግዛት የሚያሰኝ ልዩነት እንዳልነበር ያሳያል። 2) በሃይለሥላሴ ዘመንና በደርግ ዘመን ኤርትራውያን በተለያዩ የመንግሥት መዋቅር እየተንቀሳቀሱ በመሥራት ከማንም ኢትዮጵያዊ የበለጠ እንጂ ያላነስ ሚና የያዙ እንደነበሩ የማይካድ ሓቅ ነው።

ለዚህም ዋና ማስረጃ ፕሮፌሰሩ ራሳቸው በሃይለሥላሴ ዘመንና በደርግ ዘመን ከፍተኛ ባለ ስልጣን እንደነበሩ የማይክዱት ሓቅ ነው። በተጨማሪም መጥቀስ ካስፈለገ፣ እኔ ልጅ ሆኘ የዓድዋ ኣገረ-ገዥ ኮሎኔል (ኋላ ጀነራል) ኢሳያስ ገ/ሥላሴ የተባሉ ኤርትራዊ ሰው ነበሩ። ከሳቸውም ሌላ ብዙዎች ኤርትራውያን በመላው የሃገር ኣገዛዝ፣ እስከ ምኒስተር ደረጃ፣ በጦር ሃይሎችም ከጀነራል ኣንስቶ እስከ ተራ ወታደር፣ እስከ መጨረሻውም የርእሰ-ብሔር ቁንጮ የወጡት ጀነራል ዓምዶምን ብንወስድ፣ በፍጹም ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች የሚባለው ነገር ምንም የማያከራክር ውሸት መሆኑን ለማየት ይቻላል።
ይህንን የማይቀበል ሰው ካለ፣ ኣንዲት ኣፍራሽ የምትሆን ማስረጃ ሊያርብልኝ ይችላል። ይኸውም፤ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይ፣ የስፓኛ፣ የፖርቱጋል… ወዘተ፣ ቅኝ ግዛት ከነበሩት ሃገሮች ከኣንዳቸውም ቢሆን፤ ከህንድ፣ ከናይጀርያ፣ ከኣልጀርያ… ወዘተ፣ ከቅኝ ግዛቶች ወደ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ወይ ስፓኛ ወስዶ ኣገረ-ገዢ ያደረገ ካለ፣ ለማስረጃ ቢቀርብልኝ፣ እኔ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች ብየ መቶ-በመቶ እቀበለዋለሁ። እስከዚያ ድረስ ግን ይህ ጉዳይ ምንም ኣከራካሪ እንዳልሆነ ለፕሮፌሰር በረከትና ሌሎችም የተሳሳተ ኣስተሳሰብ ለያዙ ሰዎች ሀሉ መግለጽ እፈልጋለሁ። ይህ ውሸት ከእንግዲህ ወድያ ቢያበቃ ደግ ነው።
ይህ ለኤርትራ ነፃነት ትግል ሲባል የተጠነሰሰ ሓሰት ነው ተብሎ ከታመነበት ወደፊት ለመራመድ የሚቻለው ውሸቱን ኣጋልጦ፣ በሓቅ መሰረት ተረግጦ ነው እንጂ ይህን ሓሰት ተመርኩዞ ወደፊት ለመሄድ ኣይቻልም። ስለዚህም ነው በዚህ ለማትኮር የፈለግሁት።
ፕሮፌሰር በረከት ሃብተሥላሴ በመቀጠል፤ የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ በኮንፌድሬሽን ኣብሮ ሊኖር ምኞትና ተስፋ ያላቸው መሆኑን በተደጋጋሚ ገልጸዋል። ይህም በጣም ደስ የሚል ሓሳብ ቢሆንም እንኳን፣ ይህንን የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበርን የሚባለውን ሓሰት እያድበሰበሱና፣ ‘ኣከራካሪ ጉዳይ ነው’ እያሉ በማንሸራሸር ኣንድነት ሊገኝ ፈጽሞ ኣይቻልም። ዘላቂ ኣንድነት ሊገኝ ከሆነ በሓቅ የተመሰረተ ኣንድነት መሆን ኣለበት። ፕሮፌሰሩ የሕግ ምሁርና ሊቅ ናቸው፣ እሳቸው ይህንን ነገር ሓሰት ነው ብለው ካላወገዙት፣ ያልተማረው ምሃይም ሰውማ ሓቅ ነው ብሎ ነው የሚቀበለው።
ኤርትራ ኣሁን ለገባችበት ዓዘቅት ምክንያቱ ይህንን እና ሌሎችም ብዙ መሰረት የሌላቸው ሓሰቶች ይዛ በመነሰቷ ነው። ቅኝ ግዛት የሚባለው ሓሰት የተጀመረው ቀንድ ያበቅልና፣ ቅኝ ግዛት ብቻ ሳይሆን ለነፃነት መውጣት በተካሄደው ምርጫ ላይ ደግሞ፣ ኣማራጮቹ፤ “ነፃነት ወይም ባርነት” የሚሉ ነበሩ። ይህም ማለት ኤርትራ በኢትዮጵያ ቅኝ ከመገዛቷዋም ታልፎ፣ ኤርትራውያን ምንም መብት እንደሌለው ሰው፣ “ባርያ” ነበሩ የሚል ዓይን ያወጣ ውሸት ለምርጫ እንዳቀረቡት መታወቅና ሓሰትነቱን ኣምኖ መቀበል ያስፈልጋል።
እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ሓሰቶች እንደፕሮፌሰሩ ለመሰሉት ሰዎች ኣከራካሪ መሆን ኣይገባቸውም። ፕሮፌሰር በረከት በነበራቸው ልዩ ሚና፣ ማለትም እስከ ኣገረ ገዢነትና እስከ ምክትል እንደራሴነት መዓረግ ተሾመው በኢትዮጵያ ያገለገሉ በመሆናቸው፣ የእነዚህ ነገሮች ሓሰትነት በግልጽ ለማስረዳ የሚችሉ እና፣ የኢትዮጵያ ሕዝብና የኤርትራ ሕዝብ ከነበረው ስርዓት ስር እኩል ይገዙ እንደነበሩ፣ የኤርትራ ሕዝብም ከሌላው ብሔር የቀለለ እንጂ ምንም የከበደ ጫና እንዳልደረሰበት፣ ይልቅም ሌሎች ብዙ ብሔሮች የባሰ ቀምበር የተጣለባቸው እንደነበሩ ሓቁን መግለጽ የሚገባቸው ሰው ናቸው። ይህንን ግን ኣላደረጉም። ይባስ ብሎ፣ ከፕሮፌሰሩ ተደጋግሞ የተሰማው፣ “ንጉሡ ፌዴረሽኑ ቢፈርስ ምን ይመስልሃል ብለው ጠይቀውኝ፣ ‘ጃንሆይ፣ ይህ የተኛውን ኣንበሳ መቀስቀስ ነው’ ኣልኳቸው…” እያሉ ስለ ኤርትራ ሕዝብ ኣንበሳነት ለመናገር የተነሱ ነው የሚመስሉ። ይህም ኣዲስ ነገር ሳይሆን፣ ዘወትር ኤርትራውያን ራሳቸውን ለማታለል የሚሉት ሓሰት ነው። ሓቁ ግን ኣንበሳ በራሱ ሓሳብ የሚመራ እንጂ በሌላ እንሰሶች የማይመራ ፍጡር ሲሆን፣ ኤርትራውያን ግን መላው የነፃነት ትግላቸው እንደሚመሰክረው የግብፅ፣ የሊብያ፣ የሶርያ፣ የዒራቅ፣ የሌሎችም የዓረብ መንግሥታት ኢትዮጵያን ለማዳከም መሣርያ ኣድርገው እንደተጠቀሙባቸው ሓቅ እንጂ ምንም የሚያጠያይቅ ጉዳይ ኣይደለም። ኢትዮጵያም እጆችዋን ወደ እግዚኣብሔር ኣንስታ በእነዚህ የዓረብ መንግሥታት መሪዎችና ሕዝቦች የደረሰና የሚደርስም ያለው ፍርድና ቅጣት ዓይን ላለው ሁሉ ግልጽ ነው። ይህ ለኤርትራም ሕዝብ የሚተርፍ ያለ ይመስላል ።

ይቀጥላል,..
ገ/ኢ. ጐርፉ።